የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 12
ADDIS ABABA, 13th January, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፮/፪ሺ፲፯ ዓ.ም
የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ …………....ገጽ ፲፯ሺ፬፻፲፭

**Content**

Proclamation No. 1346/2024
Government Bond Proclamation ..…. Page 17415

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፮/፪ሺ፲፯

## ስለ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች የወጣ አዋጅ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰዱትን ብድር ለመክፈል ባለመቻላቸው ዕዳውን መንግሥት ተረክቦ የእዳው ክፍያ በመንግሥት ዕዳ ሰነድ (ቦንድ) እንዲከፈል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ለማሳደግ የሚውለው ገንዘብ በመንግሥት ዕዳ ሰነድ እንዲከፈል ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፮/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 1346/2024

## PROCLAMATION ON GOVERNMENT BOND

**WHEREAS**, it has become necessary to issue government bond to be used for repayment of loan granted by the Commercial Bank of Ethiopia to public enterprises which have failed to repay such loan;

**WHREAS**, it has become necessary to issue Government Bond to be used for raising the capital of the Commercial Bank of Ethiopia;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Government Bond Proclamation No. 1346/2024".

**፪. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር፡-

፩/ ተጠቃሚው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሆነበት ፱፻ ቢሊዮን ብር (ዘጠኝ መቶ ቢሊዮን ብር) ዋጋ ያለው የመንግሥት ዕዳ ሰነድ እንዲያወጣ፤

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚያወጣው የመንግሥት ዕዳ ሰነድ ውስጥ፡-

ሀ) ፰፻፵፭ ቢሊዮን ፫፻፲፮ ሚሊዮን ፭፻፸ሺ.፩፻፲፬ ብር (ስምንት መቶ አርባ አምስት ቢሊዮን ሦስት መቶ አስራ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሺ አንድ መቶ አስራ አራት ብር) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተበድረው ያልከፈሉትን ዕዳ ለመክፈል እንዲያውል፤

ለ) ፶፬ ቢሊዮን ፮፻፹፫ ሚሊዮን ፬፻፳፱ሺ.፰፻፹፮ ብር (ሃምሳ አራት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካፒታል ክፍያ ለማዋል፤በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለክፍያና ወለድ</u>

**፫. <u>ክፍያ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ መሰረት የሚወጡት የመንግሥት የዕዳ ሰነዶች ከሦስት ዓመታት የችሮታ ጊዜ በኋላ በ፲ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተከፍለው ይጠናቀቃሉ።

**2. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered:

1/ To issue Government Bond of Birr 900,000,000,000.00 (Nine Hundred Billion Birr) with the Commercial Bank of Ethiopia as beneficiary;

2/ To utilize the Government Bond issued in accordance with this Proclamation;

a) 845,316,570,114.00 birr (Eight Hundred Forty-Five Billion, Three Hundred Sixteen Million, Five Hundred Seventy Thousand, One Hundred Fourteen birr) to repay the loan extended by the Commercial Bank of Ethiopia to public enterprises but not repaid;

b) 54,683,429,886.00 birr (Fifty-Four Billion, Six Hundred Eighty-Three Million, Four Hundred Twenty-Nine Thousand, Eight Hundred Eighty-Six birr) to raise the capital of the Commercial Bank of Ethiopia.

## <u>PART TWO</u>
## <u>REDEMPTION AND INTEREST</u>

**3. <u>Redemption</u>**

Government bond issued in accordance with Article 2 of this Proclamation shall be redeemed in 10 years after a grace period of Three years.

፬. **ወለድ**

በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡት የመንግሥት የዕዳ ሰነዶች ላይ የሚከፈለው ወለድ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፭. **ከግብር እና ቀረጥ ነጻ ስለመሆን**

በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጥ ወይም ሌላ ማናቸውም ቀረጥ እና ግብር አይከፈልም።

፮. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4. **Interest**

The interest on Government Bond issued in accordance with this Proclamation shall be determined by the agreement to be reached among the Ministry of Finance, the National Bank of Ethiopia and the Commercial Bank of Ethiopia.

## PART THREE
## Miscellaneous Provisions

5. **Exemption From Taxes**

No Stamp Duty or any other tax shall be levied on any transaction or document relating to the Government Bond issued hereunder.

6. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 13th day of January, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**